ማኅበራዊ ጥናት መድረክ
Forum for Social Studies

ነሐሴ 1999 ዓ.ም. — የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች — ቁጥር 12

# የገጠር ድኅነት ገጽታዎችና የሚጠቁሟቸው የፓሊሲ እርምጃዎች

- የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው፡፡

❋❋❋

- የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል፡፡

❋❋❋

- በአዲስ አበባ (በ97.1 ሞገድ) እና በአዋሳ (በ100.9 ሞገድ) ከተሞች ኤፍ.ኤም. ራዲዮ ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል፡፡

❋❋❋

- በድረ-ገጹ በልማት ዙሪያ ውይይቶችን ያካሂዳል፡፡

❋❋❋

- በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን፡፡

## 1. መግቢያ

በኢትዮጵያ የገጠር ድኅነት በመጠንና በጥልቀት ሰፊ ስርጭት እንዳለው ይታወቃል፡፡ ለዚህም በምክንያትነት የሚጠቀሱት ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት፣ የመሬት መሸርሸር፣ በተለያዩ ምክያቶች አማካኝነት የሚከሰተው የእህልና የከብት ምርት መቀነስ፣ የመሬት የማረሻ በሬና የሰው ጉልበት እጥረት ናቸው፡፡ በቅርብ ጊዜ በወጣ መረጃ መሠረት በገጠር ከሚገኙት ቤተሰቦች ውስጥ ወደ አርባ ስምንት ከመቶው በድኅነት ክፍል ውስጥ ይመደባሉ፡፡

ይህ የፓሊሲ ፍሬ ሀሳቦች ጽሑፍ በተወሰኑ የአገሪቱ የገጠር ክፍሎች በተደረጉ ሁለት ገላጭ (qualitative) ጥናቶች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ እነዚህ ጥናቶች የገጠር ድኅነትና ባሕርይ፣ የሚከሰቱበትን ምክንያቶችና ሂደቶች እና ድኅነትን የመቋቋሚያ ስልቶች ላይ ያተኩራሉ፡፡ ይህ የገጠር ድኅነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ የፓሊሲ እርምጃዎችንና ክፍተቶችን ይጠቁማል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

## 2. የጥናቶቹ ዓላማዎች

ለዚህ ጽሁፍ መሠረት ከሆኑት ሁለት ጥናቶች ውስጥ አንደኛው ሰሜን ሸዋ ባሉ ሁለት ቀበሌዎች ውስጥ የገጠር ድኅነት ላይ የተደረገ ሲሆን ሁለተኛው በዋግ ሐምራ ዞንና በደቡብ ወሎ በሚገኙ ሁለት ቀበሌዎች ውስጥ በአስከፊ ድኅነት ላይ የተደረገ ነው፡፡ የጥናቶቹ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው ፡፡

ሀ) የገጠር ድኅነትንና (Poverty) አስከፊ ድኅነትን (Destitution) ባሕርይና መነሻዎች መዳሰስ፣

ለ) የማምረቻ መሣሪያዎች ለምርታማነትና ለድኅነት ያላቸውን እንደምታ መግለጽ፣

ሐ) የገጠር ቤተሰቦች በምን ዓይነት ሂደት ወደ ድኅነት እንደሚገቡ፣ ድህነትን እንዴት እንደሚቋቋሙና ከድህነት እንዴት እንደሚወጡ ማብራራት፣

መ) የህብረተሰቡ የመረዳዳት ልማዶች ከገጠር ድኅነት ጋር ያላቸውን ግንኙነት መግለፅ፣

## 3. የጥናቶቹ ስፍራዎችና ዘዴዎች

በገጠር ድህነት ላይ ያተኮረው ጥናት የተከናወነው በጣርማ በር ወረዳ ከደብረሲና ከተማ በስተሰሜን አምስት ኪ/ሜር ርቃ በምትገኘው በወይና ደጋማ ቀበሌና ከጣርማ በር ከተማ ጥቂት ኪ/ሜትሮች ርቃ የምትገኝ ቆላማ ቀበሌ ውስጥ ነው ፡፡ ሁለተኛውና በገጠር አስከፊ ድህነት ዙሪያ ያጠነጠነው ጥናት የተከናወነው በዋግ ሐምራ ዞን ሰቆጣ ወረዳ ውስጥ የምትገኝ ወይና ደጋማ ቀበሌና በደቡብ ወሎ ዞን ቃሉ ወረዳ የምትገኝ ቆላማ ቀበሌ ውስጥ ነው፡፡

ለጥናቶቹ መረጃ ለመሰብሰብ የዋሉት ዘዴዎች የአካባቢው ህዝብ አመለካከትና ተለምዶ ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ የጥናቶቹ ዘዴዎች ዓይነት ሐተታዊ (qualitative) በመባል የሚታወቅ ሲሆን እነዚህም ከቀበሌ ሹማምንቶች ጋር የተደረጉ ቃለ መጠይቆችን፣ ከተለያዩ

በዓታ፣ በዕድሜና በኢኮኖሚ ደረጃ ከሚለያዩ የቀበሌ ነዋሪ ዎች ጋር የቡድን ውይይቶችና በያንዳንዱ የጥናት ቀበሌ እስከ ዘጠኝ ከሚሆኑ የቤተሰብ አባ/እማወራዎች ጋር የተካሄዱ ጠለቅ ያሉ ውይይቶችን ያካትታል::

## 4. የጥናቶቹ ዋና ዋና ግኝቶች

### *4.1 የድሀው ክፍል ባሕርያትና መጠን (በአካባቢ ነዋሪዎች አመለካከት)*

በሰሜን ሸዋ ባሉት ቀበሌዎች በድኅነት ውስጥ ያለው የህብረተሰብ ክፍል "ድሀ"፣ "ሙያተኛ" "በጉልበቱ የሚኖር" በሚሉት አጠራሮች ይገለፃል:: በአካባቢው ነዋሪዎች አገላለጽ በዚህ የህብረተሰብ ክፍል ውስጥ የሚገ ኙ ቤተሰቦች በአብዛኛው የማረሻ በሬ የሌላቸው ሆነው አንድ ሌላ የቀንድ ከብትና ጥቂት በጎች ያሏቸው ናቸው:: የመሬት ይዞታቸውም ዝቅተኛ ምርታማነት ያለው ሲሆን መጠኑም ከግማሽ ሄክታር ላይበልጥ ይችላል:: ከግብርና የሚያኙት ገቢም ስለማይበቃቸው በተለያየ ዓይነት የቀን ስራ ይሳተፋሉ:: ይህ የድሀው ክፍል ሰሜን ሸዋ ባለው አንደኛው የጥናት ቀበሌ ካሉት ቤተሰቦች ውስጥ አምሳ በመቶ ያህል ሽፋን ሲኖረው፣ በሌላኛው የጥናት ቀበሌ ደግሞ ሰላሳ በመቶ ያህል ይደርሳል:: በአንፃሩ በአስከፊ ድህነት ውስጥ ይገኛሉ

ተብለው የሚታሰቡት የህብረተሰብ ክፍሎች በሰሜን ሸዋ "ቤት የዋለ"፣ "የማይሰራ" ተብለው ሲጠሩ ዋግ ሐምራና ደቡብ ወሎ ደግሞ "ድሀ" እና "ችግረኛ" በመባል ይታወቃሉ:: ይህ የህብረተሰብ ክፍል መሬት የሌላቸው፣ ጉልበት አጠር የሆኑ፣ በሴትና አዛውንት የሚመሩ ቤተ ሰቦችን ያቅፋል:: እነኝህ በአስከፊ ድኅነት ውስጥ ይገኛሉ የሚባሉ ቤተሰቦች ከአንድ ዓመት ውስጥ ካሉት አብዛኛዎ ቹ ወራት የምግብ እጥረት ሲያጋጥማቸው የተሟላ ቤትና ልብስ የሌላቸው ናቸው:: በመሬትና ከብት ዕጥረት ምክንያት የሚተዳደሩትም ያችውን ትንሽ መሬት በማከራየትና እንደ እንጨት፣ ከሰልና የእጅ ሙያ ውጤቶችን በመሸጥና በቀን ስራ በመተዳደር ነው:: ሰሜን ሸዋ ባለው አንዱ የጥናት ቀበሌ ነዋሪዎች አስከፊ ድኅነት ውስጥ ይገኛሉ ተብለው የሚታሰቡት ቤተሰቦች በቀበሌው ካሉት አጠቃላይ የቤተሰብ ቁጥር አስራ አምስት ከመቶ ይሆናሉ::

### *4.2 የምርት መሣሪያዎች ይዞታና ከድኅነት ጋር ያላቸው ግኑኝነት*

በእርሻ ያለ ለተመሠረተው የገጠር ኑሮ መሬት የሰው ጉልበትና የማረሻ በሬ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች ናቸው:: በአወያየናቸው የቀበሌ ነዋሪዎች አመለካከት የመሬት ይዞታ ለገጠር ኑሮና የኑሮ ደረጃ ዋነኛ መሠረት ነው:: በሰው ጉልበት ረገድ አንድ ቤተሰብ አንድ ወንድና አንድ ሴት ያስፈልገዋል:: በሕብረተሰቡ ውስጥ ባለው በፆታ ላይ በተመሰረተ የስራ ክፍፍልና ሴቶች በቤት ውስጥ ከሚሰሯቸው ስራዎች የተነሳ የአንድ ሴት ጉልበት የማይተካ ሚና አለው:: ወንዶች በአራሽነት ካላቸው ብቸኛ ሚናና ሌሎች የምርትና የግብይት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ባላቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሳቢያ አንድ ወንድም ወሳኝ ሚና አለው:: በፍቺና በሞት ምክንያት አንድም የሚያግዛት አዋቂ ወንድ የሌላት ሴት ያላትን መሬት በማከራየት ኑሮን መወጣት ብትችልም ወደ ድኅነት የመውረድ ዕድሏ ከፍተኛ ነው:: አንድ ወይም ሁለት ልጆችም ከብቶችን በማገድና አንዳንድ የእርሻና የቤት ስራዎችን በማከናወን እጅግ ጠቃሚ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ:: ከዚህ በላይ ጉልበት ያላቸው ቤተሰቦች ደግሞ የምርት፣ የአፈር ጥበቃና የገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴ ዎቻቸውን በማጠናከር ኑሯቸውን የማሻሻል ወይም ድኅነት የመቋቋም ችሎታቸውን ያጎለብታሉ:: አራሾች እያንዳንዳቸው ጥንድ በሬዎች እንዲኖራቸው ቢመኙም በሁለት አራሾች መካከል በሚደረጉ በሬን አቀናጅቶ የማረስ የተስፋፋ ልማድ ሳቢያ ለአንድ ቤተሰብ አንድ በሬ የሚያስፈልገውን የእርሻ ስራ ለማከናወን በቂ ሊሆን ይችላል:: አንድም በሬ የሌላቸው ግን ዘር የመዝሪያ ጊዜ እየተላለፈባቸውና መሬታቸውን ለማከራየትና የማረሻ በሬ ለማግኘት ሲሉ ጉልበታቸውን ስለሚበዘብዙ የኑሮ ደረጃቸው እያሽቆለቆለ ይሄዳል:: የእነዚህን የምርት መሣሪያዎች ሚና ባጠቃላይ ስናየው ምንም ወይም አነስተኛ መሬት ያላቸውና ወይም አንድም የወንድ ጉልበት ወይም በሬ የሌላቸው ቤተሰቦች ድኅነት ውስጥ የመውደቅ ዕድላቸው የሰፋ ነው:: ነገር ግን አንድ በሬ ያላቸው ቤተሰቦች በመካከላቸው ሰፊ የሆነ የኑሮ ደረጃ ልዩነት ሊኖር ስለሚችል ያላቸው አጠቃላይ የከብት ቁጥር የተሻለ የኑሮ ደረጃ መለኪያ ነው::

### *4.3 የድኅነት ሂደት*

የገጠር ቤተሰቦች ወደ ድኅነት የሚገቡት በተለያዩ መንገዶችና ውስብስብ በሆኑ ሂደቶች ነው:: ለምሳሌ በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰተው የእህል ምርት ማሽቆልቆል የገጠር ቤተሰቦች ከሚደኸዩበት መንስኤዎች አንዱ ሲሆን ጨርሰው ወደ ድኅነት የሚገቡት ግን ይህ ክስተት በተደጋጋሚ ወይም በባሰ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው ወይም ከሌሎች አጋጣሚዎች ጋር ሲዳመር ነው:: ሌላው መሠረታዊ የሆኑት የምርት መሣሪያዎች ማለትም

መሬትና የሰው ጉልበት ወይም የማረሻ በሬ እጥረት እላይ የተገለጸው ደረጃ ሲደርስ ቤተሰቦች ወደ ድኅነት ይወድቃሉ፡፡ የባለትዳሮች ፍቺና የአባ ወራው ሞት ንብረትና የወንድ ጉልበት ሲለሚያጎድል ሴቶችንና ልጆቻ ቸውን አፋጣኝ በሆነ ወይም በተራዘመ ሂደት ወደ ድኅነት ሊከታቸው ይችላል፡፡ ሌሎች ከቤተሰቡ አመሰራ ረትና ዕድገት ጋር በተያያዙ ሂደቶች ተጽዕኖ የሚደርስባቸው ለምሳሌ በቅርብ የተመሠረቱ ቤተሰቦች በዚኽም ምክንያት የመሬት ክፍፍል ውስጥ ለመሳተፍ ያልበቁ ቤተሰቦች፣ የልጆች ቁጥር ያለልክ ከፍ ያለባቸው ቤተሰቦች እና በአዛውንት የሚመሩ ቤተሰቦች ጊዜያዊ ወይም ቋሚ ለሆነ ድኅነት ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ክስተቶች ድኅነትን የሚያስከትሉት ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ብቻ ሳይሆን በተራዘመ ሂደትና ተደራርበው ሲመጡ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ የእህል ምርት መቀነስ ከአባ ወራው ሞት ወይም መታመም ጋር ሲያያዝ ድኅነትን ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡

## 4.4 ድኅነትን መቋቋም

ድኅነትን ሊያስከትሉ የሚችሉ ገጠመኞችን በመቋቋም የኑሮ ደረጃቸውን ለመጠበቅ የሚችሉ ቤተሰቦች በርካታ ናቸው፡፡ ይህንን ለማድረግ ከሚያስችላቸው ሁኔታዎች አንዱ ከመጀመሪያውም ጠንካራ የኑሮ ደረጃ ሲኖራቸው ነው፡፡ ሌላው ደግሞ በግብርናና ከግብርና ውጪ ያሉትን የገቢ ምንጮቻቸውን ማብዛት ወይም ማሰበጣጠር ሲችሉ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ በቂ የሆነ የጉልበትና የሙያ ወይም የንግድ ችሎታ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡

ድኅነትን ማስቀረት ያቃታቸው ቤተሰቦች ደግሞ በድኅነት ውስጥ ሆነው ኑሮን ለማሸነፍ የተለያዩ አነስተኛ እንቅስቃሴዎች ያደርጋሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በግብርና ውስጥ እና ከግብርና ውጭ ያሉ የቅጥር ስራዎች፣ የእንጨትና የከሰል ሽያጭ፣ ምግብ ለስራና ካሉበት ማህበረሰብ የሚገኙ የገንዘብና የእህል ብድሮች ይገ ኙበታል፡፡ እነዚህ የገቢ ምንጮች ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮ ለመምራት እንጂ ከድኅነት ወጥቶ የተሻለ የኑሮ ደረጃ ላይ ለመድረስ የሚያስችሉ አይደሉም፡፡

## 4.5 ከድኅነት መውጣት

ድኅነት ውስጥ የነበሩ አንዳንድ ቤተሰቦች በከባድ ጥረትና የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ከድህነት አረንቋ ለመውጣትና የተሻለ ኑሮ ለመምራት የሚችሉ አሉ፡፡ ከእነዚህ ስልቶች አንዱ ለግብርና ትኩረት በመስጠትና የሚገኘውን ትርፍ ከብቶች ለመግዛት በመጠቀም የቤተሰቡን የኢኮኖሚ ደረጃ በማሳደግ ነው፡፡ ለዚህ ስልት ስኬታማነት የእርሻውንና የከብት ዕርባታ ዘርፎችን መደጋገፍ ሲጠይቅ በቂ የሆነ የመሬት ይዞታ፣ የሰው ጉልበትና አመርቂ የሆነ የእህል ምርት ያሻዋል፡፡ ሁለተ ኛው ዓይነት ስልት ደግሞ በግብርናና ከግብርና ውጭ ባሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በመሳተፍ የቤተሰቡን ሀብት ማደራጀት ነው፡፡ ይህ ስልት ከፍተኛ የሆነ ክህሎትና የሰው ጉልበት ይጠይቃል፡፡ አንዳንድ ቤተ ሰቦች ከማህበረሰባቸው በሚያገኙት የእህል፣ የበሬና የሰው ጉልበት እርዳታና ከተማ በሚኖሩ ዘመዶቻቸው ዕርዳታ የራሳቸው ጥረት ተጨምሮበት ከጊዚያዊ ድኅነት የሚላቀቁበት መንገድ አለ፡፡ በተጨማሪም ዕቁብን ጨምሮ የቁጠባ ልማድና እንደ ርቢና መቀናጆ ያሉ ሁለት ቤተሰቦች ተረዳድተው ከብት የሚያረቡበትና መሬታቸውን የሚያርሱበት ባሕላዊ ልማዶችን በአግባቡ በመጠቀም ድኅነትን ማሸነፍ የሚችሉ አሉ፡፡

## 4.6 በጥናቶቹ ላይ የተመሰረቱ የፓሊሲ ጥቆማዎች

ከላይ የተገለጹት ጥናቶች በተወሰኑ አካባቢዎች ስለ ሕብረተሰቡ አመለካከትና ተለምዶ ሐተታዊ (qualitative) ምርምር በማድረግ ስለ ገጠር ድኅነት ባሕርይና ተጓዳኝ ሂደቶች ያለንን ግንዛቤ ለማጎልበት ሞክረዋል፡፡ ይህም በአሁኑ ጊዜ እየተተገበረ ባለው የድኅነት ቅነሳ ፓሊሲና ጥረት ውስጥ ሊታከሉበትና ሊያጠናክሩት የሚችሉ ፍሬ ሐሳቦችን ይጠቁማል፡፡ የሚከተለው ክፍል የነዚህን ዓይነት የፓሊሲ ፍሬ ሐሳቦች ይዘረዝራል፡፡

ሀ/ በድርቅና በሌሎች ምክንያቶች የሚከሰተውን የእህል ምርት መጠንና የከብት ይዞታ መቀነስን በተሻለ ሁኔታ መቋቋም ቢቻል ድኅነትን በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ ሚና ሊጫወት እንደሚችሉ የሚያጠራጥር አይደለም ፡፡ ከዚህ አኳያ ድርቅን ለሚቋቋሙና ቶሎ ደራሽ ለሆኑ የእህል ዝርያዎች፣ ለተቀናጁ የሰብል ተባዩች መከላከያ ስልቶችና ለውሃ ማቆር ስልቶች (የማጥመ የፓሊሲ ፍሬ ሐሳቦች ቁጥር 7 ይመልከቱ) ተገቢ የሆነ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

ድርቅ በሚከሰትበት ጊዜ የገጠሩ ሕብረተሰብ የከብት ሀብቱን ጎጂ በሆነ ሽያጭና በሞት እንዳያጣ የከብት ግዢ ፕሮግራሞችንና በድርቅ ለተጎዱ ቤተሰቦች ለዘርና ለማረሻ በሬ የሚሆን ዕርዳታና ብድር በሰፊው ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የእህል

ሰብል ጥፋት የሕመምና ሌሎች አደጋዎች ለገጠሟቸው ቤተሰቦች የኑሮ ዋስትና ወይም የኢንሹራንስ አገልግሎት በስፋት ማቅረብ ድኅነትን በመከላከል ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽ ማድረግ ይችላል::

ለ/ የገጠር ቤተሰቦች በእጃቸው ያለውን ንብረት እንዲያዳብሩ ማስቻል ማለት ድኅነትን እንዲቋቋሙ ማስቻል ማለት ነው:: ይህን የማድረጊያ አንደኛው ዓይነትና ስልት የብድር አገልግሎት ነው:: አሁን እየተሰጠ ያለው የብድር አገልግሎት ከህዝብ ፍላጎት ጋር በተሻለ ሁኔታ እንዲጣጣም ማድረግ ያስፈልጋል:: ይህ ደግሞ የብድር አገልግሎቱን ማስፋት የንብረት ዋስትናውን መጠን መቀነስ እና የብድር መጠኑን አላማውንና የክፍያ ጊዜዉን በደምበኞች ፍላጎት ላይ መመስረት የግድ ይላል:: የብድር አገልገሎት ከቁጠባና የዋስትና አገልግሎቶች ጋር ተቀናጅቶ ቢሰጥ የበለጠ ውጤታማ ሊሆን ይቻላል:: እነዚህ አገልገሎቶች መሬት አጠር ወይም መሬት የለሽ ለሆኑ፣ የማረሻ በሬ ለሌላቸውና በሴቶች ለሚመሩ ቤተሰቦች ልዩ ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል::

ሐ/ የገጠር ድኅነትን አስተማማኝ በሆነ መንገድ ለመቀነስ ሌላው ዋነኛ ዘዴ ስራ ፈጠራን በከፍተኛ ደረጃ ማጠናከር ነው:: የገጠሩ ኢኮኖሚ ከግብርና ውጪ ስራ የመፍጠር አቅሙ አነስተኛ ስለሆነ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ የስራ ፕሮጀክቶች አስፈላጊና ቀጣይ የሆነ ሚና ይኖራቸዋል:: ነገር ግን አቀራረፃቸውንና አተገባበራቸውን ማሻሻል ድኅነትን በመቀነስ ረገድ ያላቸውን ውጤታማነት ያጠናክረዋል:: ለምሳሌ የክፍያዎችን መጠን ማሻሻል፣ ተጨማሪ ስራ መፍጠር ለሚያስችሉ ፕሮጀክቶች፣ ለፕሮጀክት ውጤቶች ጥራትና ለተሳታፊዎች የሙያ ክህሎቶችን ለማስተላለፍ በቂ ትኩረት መስጠት ያሻል::

ከስራ ፈጠራ ፕሮጀክቶች ይልቅ ገበያውን መሠረት ያደረጉ እንቅስቃሴዎችን ማጠናከር የበለጠ ዘለቄታማነት ይኖረዋል:: ለዚህ አላማም የገበያን ፍላጎት መሠረት ያደረጉና ጥራት ያላቸው የሙያ ስልጠና ፕሮግራሞችን ማስፋፋት፣ የብድርና ቁጠባ አገልግሎት ጋር ማስተሳሰረና በሙያ ውጤቶች ሽያጭ ውስጥ የህብረት ሥራ ማህበራትን ሚና ማጠናከር ፋይዳ ይኖረዋል:: እንደ እነዚህ ካሉ በቤተሰብ ደረጃ ከሚደረጉ ጥረቶች በተጨማሪ የገጠሩን ኢኮኖሚ ለማጠናከር የሚወሰዱ እርምጃዎች ወሳኝ ናቸው :: ለምሳሌ የገጠር መንገዶችና ትራንስፓርት ማጠናከርና ለገጠር ከተማዎችና ገበያዎች ዕድገት አስፈላጊ ለሆኑት ፓሊሶዎች የመሠረተ ልማት ግንባታና የግል ባለሀብቶች ተሳትፎ በቂ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል:: በተጨማሪም የገጠር ቤተሰቦች በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች እየተዘዋወሩ መስራት እንዲችሉ በቂያቸው በሌሉበትም ጊዜ የመሬት ይዞታቸው እንዲጠበቅላቸው የመሬት ፓሊሲ ማስተካከያ ማድረግና በግል ባለሀብቶች የሚንቀሳቀሱ እርሻዎች እንዲስፋፉ ድጋፍ መስጠት ይበጃል::

**(ያሬድ አማረ፣ ዶ/ር)**

**ምንጮች:-** Yared Amare. 2002. Rural *Poverty in Ethiopia: Household Case Studies from North Shewa*. FSS Discussion Paper No. 9. Addis Ababa: FSS.

Yared Amare. 2003. *Destitution in the Northeastern Highlands of Ethiopia: Community and Household Studies in Wag Hamra and South Wollo*. FSS Studies on Poverty No. 3. Addis Ababa: FSS.

**Acknowledgement & Disclaimer**

*This document has been produced with the financial assistance of the European Union. The contents of this document are the sole responsibility of the author and can under no circumstances be regarded as reflecting the position of the European Union.*

**አድራሻ: የማኅበራዊ ጥናት መድረክ ♦ ፖ.ሳ.ቁ 25864 ኮድ 1000 ♦ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**
**ስልክ: 011-157 29 90/91 ♦ ፋክስ: 011-157 29 79**
**ኢሜይል: fss@ethionet.et ♦ ድረ ገፅ: www.fssethiopia.org.et**